ማስታወቂያ

ቀን 09/01/2019 ዓ.ም

ለአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የ2019 ዓ.ም መደበኛ ቅድመ ምረቃ እና ድህረ ምረቃ አዲስ ገቢ እና ነባር ተማሪዎች በሙሉ

የ2019 ዓ.ም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የመግቢያ ፈተና ወስዳችሁ ያለፋችሁ እና በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የተመደባችሁ ተማሪዎች በሙሉ እንኳን ደስ አላችሁ እያልን፤ **የአዲስ ገቢ እና ነባር መደበኛ ቅድመ ምረቃ እና ድህረ ምረቃ ተማሪዎች** ወደ ዩኒቨርሲቲ የመግቢያ ቀን እንደሚከተለው እናሳውቃለን።

- ምዝገባው የሚከናወንበት ቀን **መስከረም 20 እና 21/2019 ዓ.ም** ሲሆን
- ለአዲስ ገቢ ተማሪዎች ገለፃ (Orientation) የሚሰጥበት ቀን **መስከረም 22/2019 ዓ.ም** ከጠዋቱ 3፡00 ጀምሮ ይሆናል
- እንዲሁም በቅጣት የመመዝገቢያ ቀን **መስከረም 22/2019 ዓ.ም** ሲሆን ትምህርት የሚጀመረው **መስከረም 25/2019 ዓ.ም** መሆኑን እየገለፅን።

አዲስ ገቢ ተማሪዎች ለምዝገባ በምትመጡበት ጊዜ፡-

1. የትምህርት ማስረጃ ዋናውንና ፎቶ ኮፒ
   - የ12 ክፍል ብሔራዊ ፈተና ሰርቲፊኬት
   - ከ9-12 ክፍል የተማራችሁበትን ትራንስክሪፕት
2. 4 ፓስፖርት ሳይዝ ፎቶ ግራፍ
3. አንሶላና ብርድ ልብስ
4. የስፖርት ልብስና ጫማ ይዛችሁ እንድትመጡ እያሳወቅን ከላይ ከተጠቀሱት ቀናት ውጭ ቀድሞም ሆነ ዘግይቶ የሚመጡትን ተማሪዎች የማናስተናግድ መሆናችንን እንገልፃለን።

ማሳሰቢያ፡- የክረምት ኢንተርንሽፕ ላይ ያላችሁ ተማሪዎች **መስከረም 11/2019 ዓ.ም** ሪፖርት እንድታደርጉ እናሳስባለን።

ለተጨማሪ መረጃ የዩኒቨርሲቲውን ድህረ ገጽ www.astu.edu.et ይጎብኙ።

የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ

ሬጅስትራር እና አልሙናይ ጽ/ቤት

አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ሬጅስትራር
ዋና ሬጅስትራር
Main Registrar
Adama Science and Technology University
Registrar